EthioLion

# ወይ ፍንክች !

ጠኋት በልጅነት ፤ ቃል የገባሁለት
ኢትዮጵያዊነቱን ፤ የመሰከርኩለት
ከማንም ከምንም ፤ በልጦ የሚከበር
የእምነት ፤ እዳ አለብኝ ፤ አብሮኝ የሚቀበር ።

የጓዶች አደራ ፤ ከመቃብር ሆኖ
ይጮሃል ፤ ይጣራል ፤ ከምን ጊዜም ፤ ገንኖ
ዛሬም ፤ ታገል ይላል ፤ ጫካ ፤ ግባ ፋኖ
ሞተን ሳናልቅማ ፤ አይቀር ተወጥኖ
ጩኸት ቢበረክት ፤ አይቀርም ታፍኖ ።

አብረውኝ ተጉዘው ፤  መንገድ የወደቁ
በግፍ በጭካኔ ፤  በፋሽስት ያለቁ
ዛሬም አልደረቀ ፤  ትኩስ ነው ፤  ደማቸው
መቼ ተረሱና ፤  አፈር ቢጫናቸው
አሰሱም ፤ ገሰሱም  ፤  ይዛበትባቸው ።

ከሰማይ ከምድር ፤ የከበደ አደራ
ተሸክሞ ያለ ፤ ቋሚ ባለተራ
በደሙ የከፈለ ፤ ተነስ ሲል ፤ ሲጣራ
አርማውን አንስቶ ፤ ችቦውን ያበራ
ዛሬም ፤ ኢሕአፓ አለ ፤ ጽናቱ የሚያኮራ ።

የእምነት እዳ ፤ አለብን ፤ በአላማ ልንጸና
ሞቶ ፤ ላኖረን ጓድ ፤ ለዚያ ፤ ቆራጥ ጀግና
እውን ፤ ሆኖ ህልሙ ፤ የተዋደቀለት
ከግብ ልናደርሰው ፤ ቃል የገባንለት
አለብን አደራ ፤ ጠኋት የተዘራ
አጭደን  ፤  አልወቃነው  ፤  መች ገባ  ፤  ጎተራ ።

በታጋይ ደም ፤ ታጥቦ ፤ የጠራ ፤ የነጣ
ተስፋ የማይቆርጠው ፤ ባባጣ ጎርባጣ
እምነቱን ፤ ማተቡን ፤ ጸንቶ የዘለቀ
የኢሕአፓ ፤ ልጅ ነው ፤ ጥንትም የታወቀ።

ታግሎ መጣልና ፤ ታግሎ ፤ መውድውቁንም
የኢሕአፓ ጀግና ፤ ያውቅቀዋል ፤ ጥንቱንም
መታገል የሚሻ ፤ ታግሎ ፤ ያስመሰክራል
መቼ ፤ በአየር ሞገድ ፤ በጽሁፍ ያቅራራል
የወረቀት ነብር ፤ ያየር ሞገድ ፤ ታጋይ
ምርኮኛም ፤ ቁስለኛም ፤ አላሰየም ግዳይ ።

ፋሽስቱ ተነስቶ ፤ ዛሬ ቢንጠራራ
ተኩላ ግብራበሩን ፤ ሊያደራጅ ቢጠራ
ጩኸት ቢበረክት ፤ እሪታው ቢደራ
እነ አባ  ፤ ኮስትሬ ፤ አለን ለምንጠራ
ወይ ፍንክች ፤ ወይ ንቅንቅ ፤ ትግላችን ሳይጠራ ።

ታዛቢው … February 10, 2012

EthioLion.Com

Ethiopia Will Prevail!